# የSY25-26 እና SY26-27 የ‘Duke Ellington’ የስነጥበባት (Arts) ትምህርት ቤት: የመግቢያ-መቀበያ ሂደት የደረጃ መጠን (Admissions Process Rubric)

ለክፍል ደረጃዎች: 9-12*

**ማስታወሻ:** ይህ የደረጃ-መጠን/rubric፤ ለSY25-26 እና SY26-27 - የመግቢያ-ዑደቶች (admissions cycles) በስራ-ላይ ይውላል።

**ስለ ‘Duke Ellington’ የስነ-ጥበባት ትምህርት ቤት (Ellington) - የመግቢያ መስፈርቶች (Admissions Criteria)**: በ‘Ellington’ ውስጥ፣ ለስዕል የጋለ ስሜት ያላቸውን፣ ለማህበረሰቡ ቁርጠኝነትን የሚያሳዩ እና የስነጥበብ ዜጎችን የሚያበረታቱ፣ እና ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ውስጥ አልፈው የሚሰሩ – ጥብቅ የሆነ የኮሌድ ቅድመዝግጅት የጊዜ ሰሌዳን ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ፤ ቅድመ-ባለሙያዊ የሆነ የስዕል ስልጠናዎችን ለመውሰድ ትጋትን በማሳየት የሚሰሩ ምሁሮችን እንፈልጋለን። ምንም-እንኳን የውጤት-ደረጃቸው ወይም ያስመዘገቡት ውጤቶች ምርጥ ነው ባይባልም፤ ለሁሉም ክፍሎቻቸው - ጥረት-የሚያደርጉ፣ በይበልጥ ስኬታማ የሆኑ አመልካቾችን ማግኘት እንፈልጋለን።

**ስለ ‘Ellington’ የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** በ‘Ellington’ ውስጥ፣ ሁሉም አመልካቾቻችን፣ እንደ መጀመሪያ የማመልከቻቸው አካል አድርገው፤ ጽሁፍ (essay)፣ ሪፖርት ካርድ፣ እና ሦስት (3) የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) እንዲያስገቡ እንጠይቃለን። ‘GPA’ው በDCPS የደረጃ-አሰጣጥ ፖሊሲ (grading policy) አማካኝነት - የተሰላ/calculated-የሆነ ነው። የ‘My School DC’ ሎተሪ ማመልከቻቸውን በሚገባ ያስገቡ ሁሉም የሎተሪ አመልካቾች፤ በማቅረቢያ (audition) ውስጥ ለመካፈል ብቁ ናቸው። ለመግቢያ፤ በአነስተኛነት ሊገኝ የሚገባ (minimum) የGPA የውጤት ደረጃ (Score) የለም። ሁሉም የድጋፍ-መስጫ ይዘት/recommendation content እና የውጤት-ደረጃዎች/scores - በሚስጥር-የሚያዙ እና አመልካቾች፣ ቤተሰቦች፣ ወይም በተማሪው አሁን-በሚማርበት ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ ሠራተኞችን ወዘተ... ጨምሮ - ከማንም-ሰው ጋር የሚጋራ አይሆንም። ማመቻቻዎች (Accommodations) - ለማንኛውን የመግቢያ ሂደቱ (admissions process) ለማንኛውም የተወሰነ-ክፍል ሊጠየቅ-ይችል ይሆናል፤ እና ቤተሰቦች - ስለ ማመቻቻ አማራጮች/accommodation options ለመወያየት፣ የመግቢያ ዳይሬክተር (Admissions Director/’POC’ን - ሊያነጋግሩ-ይችላሉ።

እያንዳንዱ የማመልከቻ ሂደት ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሠረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚለካ ይሆናል። አመልካቶች፤ እንደ ግለሰቦች ሆነው የሚገመገሙ እና በትምህርት ቤቱ የስነጥበብ (arts) ፕሮግራሞች ከሚፈልጋቸው ጎን-ለጎን ሆኖ ይመዘናሉ። ሁሉም ብቁ-የሆነ አመልካቾች (በመምሪያ/department ውስጥ የሚገኙ) እኩል-የሆነ የደረጃ-መስጫዎች (rankings)ን ያገኛሉ። **የአመልካቹን የመግቢያ ሂደት (admissions process) ጋር የተገናኘ-የተወሰኑ ዝርዝሮችን እና የብቁነት ውጤቶች - በሚስጥር-የሚያዙ ይሆናል።**

| **የመግቢያ ክፍሎች (Admissions Component)** | **መለኪያ (Weight)** | **ማስታወሻዎች** |
|---|---|---|
| የሪፖርት ካርድ ምልከታ | 10 ነጥቦች | ‘Ellington’፣ እንደ የሪፖርት ካርድ ምልከታ-አንዱ ክፍል አድርጎ፣ ደረጃዎቹ/gradesን ብቻ፣ ይመለከታል። አመልካቾች፤ የመጨረሻውን የSY24-25ን እና የSY25-26 የመጀመሪያ-አጋማሽ/first quarter ሪፖርት ካርዶችን ማስገባት-ይገባቸዋል። በአነስተኛነት መገኘት የሚያስፈልገው (minimum) GPA መስፈርት አይሆንም፤ ነገር-ግን ማመልከቻው-ተቀባይነት ኖሮት - ለመግባት (admission) እንዲታይ ለማድረግ፣ ሁለቱም ሪፖርት ካርዶች መግባት አለበት።<br><br>‘GPA’ው በDCPS የደረጃ-አሰጣጥ ፖሊሲ (grading policy) አማካኝነት - የተሰላ/calculated-የሆነ ነው።<br><br>የ‘D’ ወይም የ‘F’ ውጤትን ያገኙ - በሪፖርት ካርድ/በሂደት ሪፖርቱ ላይ ያስመዘገቡ አመልካቾች፤ የበለጠ መረጃዎችን ወይም ዝርዝሮችን በቤተሰባቸው ቃለ-መጠይቅ ጊዜ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። |

ወደ 11ኛ እና 12ኛ ክፍል የሚገቡ አመልካቾች ላይ - ከስነጥበብ (arts) ትምህርት ቤት እስከተላለፉ ድረስ እና በቂ የሆነ የስነጥበባት ክሬዲቶች (arts credits) እስካላቸው ድረስ እና፣ ሊያጠኑት ካሰቡት ኮርሶቻቸው ጋር በተመሣሣይነት እስካላቸው ድረስ - ‘Ellington’ ምልከታ-እንደሚያደርግ፤ እባካችሁ አስተውሉ።

| | | |
|---|---|---|
| ጽሁፍ (Essay): በ‘My School DC’ ማመልከቻ ውስጥ | 10 ነጥቦች | በፕሮግራማችን ላይ የአመልካቹን ፍላጎት ለማወቅ፣ ለማህበረሰቡ ያላውን ቁርጠኝነት፣ እና የግል ጽናት ተሞክሮን ለማንጸባረቅ፤ ጽሁፉ (essay) - በጥቅም-ላይ ይውላል። ይህ ጽሁፍ (essay)፣ በ‘My School DC’ ማመልከቻ አማካኝነት የሚጠናቀቅ ነው።<br><br>**ማስታወሻ:** አመልካቹ እንደሚያመለክትበት ክፍል/department መሠረት-አድርጎ፤ ተጨማሪ ጽሁፎችን (essays)፣ የጽሁፍ ስራዎች (writing prompts)ን፣ ወይም ቁሳቁሶች (materials)ን - በ‘My School DC’ ማመልከቻ አማካኝነት ወይም በቀጥታ ወደ አመልካቹ - ወደሚያመለክትባቸው ክፍሎቹ (departments) በኢሜል አማካኝነት፣ እንዲያስገቡ የሚያስፈልጋቸው ሊሆን ይችላል። እነዚህ ተጨማሪ ቁሳቁሶች (materials)፣ እንደ የመደመጥ (Audition)/የፖርትፎሊዮ (Portfolio) ምልከታ ክፍል አንዱ አካል ሆኖ የሚገመገም ይሆናል።<br><br>ጽሁፎች (Essays)፤ በእያንዳንዱ የስነጥበብ መምሪያ እና የ‘Ellington’ የመግቢያ (Admissions) ቡድን ምልከታ የሚደረግበት ይሆናል። ምንም እንኳን አመልካቾች በከፍተኛደረጃ ትምህርታቸው ወቅት በሙሉ አዘውትረው መፃፍ ቢጠበቅባቸውም፣ በቴክኒካል የአፃፃፍ ችሎታዎች ላይ፤ እንደ ሰዋሰውና ቃላት (grammar and vocabulary) ላይ የጽሁፎች (essays) ግምገማ ላይ ለብቻው ያተኮረ አይሆንም።<br><br>ጽሁፎቹ (essays) - በአመልካቹ - በትምህርት ቤታችን ውስጥ፣ ለሚያመለክቱበት መምሪያ ውስጥ ለመማር የፈለጉበት ምክንያቶች ላይ ያተኩራል። እነዚህ ጽሁፎች (essays)፤ በትምህርት ቤታችን ውስጥ ለመማር ላላቸው ተስፋ-በሆነው ምክንያታቸው ላይ - የበለጠ ዝርዝር ምልከታዎችን እንዲሰጥ ተብሎ-የታቀደ ነው። |
| የድጋፍ-መስጫ ደብዳቤ ምልከታ (Recommendation Letter Review) | 10 ነጥቦች | የ‘Ellington’፣ የተማሪውን በትምህርት ቤት ውስጥ ያለውን-ተሞክሮ የበለጠ ለመረዳት እና በቀለም ትምህርት የሚያገኙት ውጤቶች ይዘትን ለመስጠት፤ የአመልካቹን ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠቀማል።<br>‘Ellington’፣ ሦስት (3) የድጋፍ መስጫዎች (recommendations)ን ይጠይቃል።<br><br>ሁሉም ድጋፍ-መስጫ (recommendation) ይዘታቸው እና የውጤት-ደረጃቸው በሚስጥር የሚያዝ እና አመልካቹን፣ ቤተሰቦችን እና በተማሪው አሁን-በሚማርበት ትምህርት ቤት ያሉ ሠራተኞችን ጨምሮ - ከማንም-ጋር አይጋራም።<br><br>አመልካቾች፤ የእነርሱን ድጋፍ-መስጫ (recommendation) አገባቦችን ሁኔታ ምን-ላይ እንደሆነ ለማየት - በማንኛውም-ጊዜ - ወደ ‘My School DC’ የሎተሪ ማመልከቻቸው በመግባት/log in ማድረግ የሚችሉ እና ለድጋፍ-ሰጪዎቹ -ማስታወሻ ይልካሉ። ለድጋፍ-ሰጪዎች/recommenders እና ቤተሰቦች፤ የድጋፍ-መስጫ/recommendation ሳይገባ-ሲቀር ወይም ያልተጠናቀቀ ሲሆን - መደበኛ የሆኑ-ማስታወቂያዎች ይላካሉ። በየግል የገቡ የድጋፍ መስጫዎች (recommendations)ን በራሳቸው በኩል እንዲከታተሉ እና የድጋፍ ሰጪውን የኢሚል አድራሻዎች ትክክለኛነት እንዲያረጋግጡ፤ አመልካቾች እና ቤተሰቦች ክትትል-እንዲያደርጉ፣ በእጅጉ እናበረታታል። **ያልገቡ የድጋፍ-መስጫዎች (Missing recommendations)፣ በመጨረሻ-ላይ ዜሮ-ነጥቦችን ያገኛሉ።**<br><br>መደመጦቹ (auditions) - የማመልከቻ የማብቂያ ቀንን ወዲያውኑ ተከትሎ የሚከናወን ሆኖ በመገኘቱ፣ ድጋፍ ሰጪዎች (recommenders)፣ የሚፈለገውን የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) በቂ በሆነ ጊዜ ማዘጋጀት እንዲችሉ፣ አመልካቾች ከማብቂያው ቀነ-ገደብ ቀደም-ብለው፣ ማመልከቻቸውን እንዲያስገቡ እናበረታታለን። አስፈላጊ-ከሆነ፤ የ‘Ellington’ ሠራተኞች፣ የአመልካቹን ትምህርት ቤት በቀጥታ-በመደወል፣ ተማሪውን በተመለከተ መረጃዎችን ለማግኘት መደወል ይችላል። |

| | | |
|---|---|---|
| የመደመጥ (Audition)/የፖርትፎሊዮ (Portfolio) ምልከታ | 50 ነጥቦች | የ‘My School DC’ ማመልከቻቸውን፣ በሎተሪ ማውጫው (Lottery round) ውስጥ በተሳካ-ሁኔታ ያስገቡ ሁሉም አመልካቾች፤ በማቅረቢያ (audition) ወይም ፖርትፎሊዮ (portfolio) ምልከታ ውስጥ በአካል-ተገኝቶ (in-person) ለመካፈል ብቁ ይሆናሉ።<br><br>በተመረጠው የእነርሱ መምሪያ/department ላይ መሠረት-አድርጎ፣ አመልካቾች - ተጨማሪ ቁሳቁሶችን (materials)፤ ጉድ ፎተግራፍን ጨምሮ (ከዚህ በፊት በMy School DC’ ማመልከቻ በኩል ካልገባ)፣ ፖርትፎሊዮ (portfolio)/የስራ ናሙና፣ ወዘተ... እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ። እነዚህ ቁሳቁሶች (materials)፣ (እንደ የተፃፈ ናሙናዎች፣ ፖርትፎሊዮ፣ ወዘተ...) አመልካቹ ወደሚያመለክትበት መምሪያ (department)፣ በቀጥታ በኢሜል አማካኝነት መግባት ያለበት እና እንደ በማቅረብ-መደመጥ (Audition)/ፖርትፎሊዮ (Portfolio) ምልከታ አንዱ አካል በመሆን ይገመገማል። የእኛ የ[የማቅረቢያ ሂደቶች/Audition Procedures]ን ይህም-ተጨማሪ አመለካከቶችን - በእያንዳንዱ የመምሪያ ሂደት ላይ የሚያቀርበውን፣ ተመልከቱ።<br><br>ዝርዝር የሆነ ትዕዛዛቶችን፣ የመደመጥ (Audition)/የፖርትፎሊዮ (Portfolio) ምልከታን ለማጠናቀቅ እርዳታ ወይም እንክብካቤዎች ለሚያስፈልጓቸው ማንኛውም አመልካቾች፣ መረጃን እና ቀጣይ እርምጃዎችን ጨምሮ፤ ለሁሉም አመልካቾች ይላካል። በተጨማሪም፣ እርዳታ እና ማመቻቻዎች (Support and accommodations)፣ በዓመቱ ሙሉ በ[ትምህርት ቤቱ ድህረ-ገጽ] ላይም ማግኘት ይቻላል። |
| **መደመጡን (audition) እና የማመልከቻውን ምልከታ አቀራረብን ያለፉ አመልካቾች ብቻ፣ በሂደቱ ቀጣይ እርምጃዎችን በመቀጠል እንዲያከናውኑ ይጋበዛሉ።** | | |
| የመምሪያው የማቅረቢያ ምሽት (Department Presentation Night) | መሣተፍ አስፈላጊ-ሆኖ የተቀመጠ አይደለም፣ ነገር ግን በእጅጉ-ይመከራል | የመምሪያው የማቅረቢያ ምሽት (Department Presentation Night) አላማው፤ መደመጣቸውን (audition) ያለፉ ቤተሰቦችን እና አመልካቾች፣ ከመምሪያ ጋር ተገናኝተው ለመምሪያው-ልዩ-ሆነው የሚጠበቁባቸውን ለመመልከት እና በዚያ ዙሪያ ስላለው ጥናት ጥያቄዎች ለመጠየቅ ዕድል-የሚሰጣቸው ነው። |
| የቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ | 10 ነጥቦች | ‘Ellington’፣ ለፕሮግራማችን የጋለ ስሜት ያላቸውን፣ ለማህበረሰቡ ቁርጠኝነትን የሚያሳዩ፣ እና ጽናትን ማሳየት የሚችሉ አመልካቾችን ለይቶ ማውጣትን አበክሮ ያምንበታል። አመልካቾች ወደ ቃለ-መጠይቁ፤ ከቤተሰብ አባል ጋር (ከወላጅ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ፣ ወይም ከሌላ የቅርብ የቤተሰብ አባል) ወይም ሌላ በህይወቱ ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ሰው ጋር (ለምሳሌ እንደ አሰልጣኝ፣ አማካሪ፣ ወይም የሕይወት መሪ/mentor) ጋር፤ አመልካቹን በመደበኛነት ከሚረዷቸው ጋር አብረው - በአካል-ተገኝተው (in-person) እንዲካፈሉ እንጠይቃቸዋለን።<br><br>አብሮ-የመጣው አዋቂ-ሰው ያለው ተሳትፎ፤ በውጤት-አሰጣጡ ላይ በማንኛውም መንገድ ቦታ-የሚሰጠው አይደለም። አብሮ-ሊመጣው የሚችለው አዋቂ-ሰው መሳተፍ-ባለመቻሉ ምክንያት፣ ተማሪዎች ቅጣት-አይደርስባቸውም። |
| የመግቢያ ምልከታ (Admissions Review) | 10 ነጥቦች | የቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የመግቢያ (Admissions) ኮሚቴው (ርዕሰ መምህር፣ የመግቢያ ቡድን/Admissions Team፣ ረዳት- ርዕሰ መምህራን፣ የተማሪዎች ዲን (Dean)፣ አስተማሪዎች እና/ወይም የመምሪያው መሪዎች) አጠቃላይ ማመልከቻውን የሚመለከቱ እና የመጨረሻ የብቁነት ውሳኔዎችን ለመስጠት፣ የመጨረሻ አስተያየትን ይሰጣሉ። |
| **ከመግቢያ ምልከታው በኋላ፣ ከእያንዳንዱ የስነጥበብ (art) መምሪያ ውስጥ ከፍተኛ-ውጤቶችን ያገኙ አመልካቾች፣ ብቁ ሆነው ይለያዩ።<br>ሁሉም ብቁ-የሆኑ አመልካቾች፤ በ‘My School DC’ ሎተሪ ውስጥ ለብቁነት መወሰኛ፤ አንድ-ዓይነት የሆነ የደረጃ-አሰጣጥ (በመምሪያው/department ውስጥ) - የሚያገኙ-ይሆናል።** | | |